<u>ቡና ጠጡ</u>

ከቀንዲል

አቶ ደጉ ለረጅም ጊዜ በኖሩበት ሰፈራቸው ውስጥ የሚታወቁት በታታሪ ሰራተኝነታቸውና በደማቅ ብርቱካናማ ቱታቸው ነው። ዛሬ ዛሬ ስራ፣ እድሜና ኑሮ ተደራርበው ቢያደቋቸውም ቁመናቸውና ደንዳና ሰውነታቸው መልካም ቀን ያየ መሆኑን ይስታውቃል።

ዛሬም እንደተለመደው፣ አቶ ደጉ ማልደው ከቤታቸው በመውጣት ከሰፈራቸው በቅርብ ርቀት ላይ ወደሚገኘው መለስተኛ የእንጨትና የብረት ስራ ድርጅታችው አቀኑ። አቶ ደጉ ትጉህና ታታሪ ቢሆኑም ደግነት ስለሚያበዙ በዚህ ስራ ላይ የመቆየታቸውንና የታታሪነታቸውን ያህል ሐብትና ንብረት አላፈሩም። ለዚህም ይመስላል ሁሉንም ነገር እንደአመጣጡ ለመመለስ ካላቸው ፍላጎት በመነጨ ንግግራቸው ላይ "እንደጊዜው" የሚል ቃል አይጠፋም።

"አቶ ደጉ ስራ እንዴት ነው ?"

"እንደጊዜው።"

"አቶ ደጉ የእቃ ዋጋ እንዴት ነው ? "

"እንደጊዜው።"

"አቶ ደጉ ጤንነትዎ እንዴት ነው ?"

"እንደጊዜው።"

ይህንን አባባል የሰፈሩም ሰው የደገፈው ይመስላል። ለጉዳዮች አጥጋቢ መልስ ሲያጡ፤ "እንደጊዜው አሉ አቶ ደጉ! እውነትም እንደጊዜው!" ይባባላሉ። አቶ ደጉ እንደጊዜው ሲሉ ማመላከት የፈለጉት የአየር ንብረቱን ይሁን አስተዳደሩን፤ መንግስትን ይሁን ዘመኑን በቅጡ አይታወቅም። ማንም ግድ ኖሮት ጥያቄ አቅርቦላቸው አያውቅም። በሰፈሩ የተወደዱና የተከበሩ ሰው በመሆናቸው ብቻ ጥያቄውም የተለምዶ፣ መልሱም የተለምዶ ነው፡፡

አቶ ደጉ አስፋልት ዳር የምትገኝ ድርጅታቸውን አዳሩን ጥበቃ ላይ ከነበረው ከአበራ ጋር ከፋፍተው አንዳንድ የተጀመሩና የተጠናቀቁ ስራዎችን ደጃፋቸው ላይ ደርድረው ወደ ውስጥ ተመለሱ።

"መብራት የለም እንዴ አንተ ?" አሉት አበራን ትንሽ ንዴትና ብስጭት በተቀላቀለበት ዜማ። የችግሩ ተደጋግሞ መከሰት የፈጠረባቸውን ስሜት መቆጣጠር እየተሳናቸው።

"አሁን ነው የሔደው አላቸው።" መብራቱን እሱ ያጠፋው ይመስል በጥፋተኝነት ስሜት ተይዞ ።

" መብራቱ ከትናንት ወዲያ ጀምሮ አልነበረም! ትናንት ከረፋዱ ጀምሮ የለም! ዛሬም የለም!" በመብራት ምክንያት ቀጠሮ የተዛባባቸው ደንበኞቻቸው ወቀሳና ጭቅጭቅ ሲታሰባቸው አንዳች ነገር ውርር አደረጋቸው። ሶስት ቀን ያለስራ ተከርሞ ደሞዝ ከየት ይመጣል? ኪራይ ከየት ይከፈላል ? የትምህርት ቤት ክፍያ ከየት ይወለዳል? ቀለብሰ ከየት ይሰፈራል? ሁለት አመት ሙሉ የመከራ ኑሮ ተገፋ... እስከመቼ ስራ

ሳይጠፉ ጉልበት ሳይደክም ሰው እንዲቸገር ይገደዳል!" ደማቸው ከፍ ብሎ ኖሮ ሰማይና ምድር እንደዞረባቸው ወደፊት ለመራመድ ሲሞክሩ እንደማንገዳገድ አላቸው።

አበራ ደርሶ ሊደግፉቸው ሲሞክር እጁን መንጨቅ አድርገው ይልቅ "ወንበሩን አቀብለኝ!" አሉት። ወደቤቱ ጠጋ ብለው በአንድ እጃቸው ግድግዳውን ተደግፈው በሌላው እጃቸው ወደ መሬት ያዘነበለ ፊታቸውን ከግንባራቸው ቀና አድርገው ያዙ። እንዳቀረቀሩ ስለነበር ነስራቸው ደርሶ ቁልቁል መንዠቅዠቅ ጀመረ።

"እረግ! ቀና ይበሉ ጋሼ እየነሰረዎት ነው እኮ ?" አለ አበራ የሚያደርገው ጠፍቶት

" ይልቅ ወንበሩን አቀብለኝ አልኩህ ! ውኋም በጆግ አምጣ!" ነስራቸው አላቆመም ከመሬት ወርዶ ከእንጨት ፍቅፋቂው ጋር መቀላቀሉን ቀጥሏል።

"ወሃ የለም ጋሼ ስንት ቀኑ ከጠፋ፣ ረሱት እንዴ!" አላቸው ወንበሩን እያቀበላቸው።

አንገታቸውን ቀና ለማድረግ እየሞከሩ "አሁን እስኪ ወዴት ይደረሳል? ለማንስ አቤት ይባላል? ምንስ ይሻላል?" አሉ በጭንቀት። "በል እስኪ ከጎረቤትም ቢሆን ጠይቀህ አምጣ" አሉት። ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ በራሱ ጊዜ በጭንቅላታቸው ውስጥ የሚብላላውን ሃሳብ እያመነዠኩ።

"ጎረቤትም የለም እኮ ጋሼ ባይሆን የላስቲክ ውሃ ልግዛ?" አለና ለጥያቄው መልስ ሳይጠብቅ ከፊታቸው ወደሚገኘው ሱቅ ገሰገሰ።

በርቀት ይሰማ የነበረው ድምጽ እየጎላ እየጎላ መጥቶ በቅጡ መደመጥ ጀመረ። ድምጹ የሚመጣው ለኢህአዴግ ቅስቀሳ ከሚያደርገው ሚኒባስ ነበር። የሚኒባሱ ታርጋ ጭቃ በመለወሱ የግል ይሁን የመንግስት አይለይም። "... አገራችን ኢትዮጵያ በልማት ጎዳና እየገሰገሰች ነው! ግስጋሴውን ለማስቀጠል ልማታዊውን መንግስትን ይምረጡ ! ንብን ይምረጡ! ተቃዋሚን መምረጥ የተጀመረውን ልማት፤ እድገትና ሰላም ማደናቀፍ ነው..." በአንድ ፈርጁ የልማት ልፈፋው፤ በሌላ ፈርጁ ዛቻ አዘል ማስጠንቀቂያው እንደቀጠለ ሚኒባሱ እንደአመጣጡ አልፎአቸው እየራቀ እየራቀ ከጆሮቸውና ከአይናቸው ተሰወረ።

"ድንቄም ልማት ¡ ድንቄም እድገት ¡ ወኋ የለሽ፣ መብራት የለሽ፣ የእውር-ድንበር ልማት!" አሉ እንዳቀረቀሩ።

አበራ ውኋውን ይዞ ተመልሶ ኖሮ የሚያደርገው ጠፍቶት ከጎናቸው ተገትሮ ቀረ።

"ምን ይገትርሃል! ውኋውን ወዲህ በል።" ብለው ውኋውን ተቀብለው በሰፊና ሻካራ መዳፋቸው ላይ ውኋውን እየቀዱ ግንባራቸውን ጠበጠቡ። መሃረባቸውንም አውጥተው ካራሱ በኋላ መሐረቡን ስርናቸው ስር አድርገው ከአንገታቸው ቀና አሉ። ንዴታቸው ጋብ ሲል ነው መሰል ነስሩም ጋብ አለ።

"ለመሆኑ ትናንት ቀበሌ ሔደህ የማዕዘን ብረት እንድንገዛ ለጅንአድ የትብብር ደብዳቤ አጽፍልኝ ብዬህ አልነበረም? ምን አደረግክ?" ጠየቁት።

"ሄጄ ነበር ጋሼ ማመልከቻውን አንቀበለም አሉኝ።"

"ለምን አንቀበልም አሉህ?" መልስ አልጠበቁም "ታድያ ምክንያታቸውን አልጠየቅከም?" ንዴታቸው ስለጨመረ በድጋሚ እንደማዞር አላቸው። ነስሩም እንዳይመለስ ስለሰጉ ተመልሰው ተቀመጡ።

“የትብብር ደብዳቤ የሚሰጠው በአነስተኛና ጥቃቅን ለተደራጁ ብቻ ነው አሉኝ።”

ህምምም .... አቶ ደጉ ቆዘሙ።

አበራ ምን አንዷል እንደፈለጉ ስላልገባው ትከሻውን ሽቅብ ሰብቆ ቆመ።

አቶ ደጉ ሳይስቁ “ወደው አይስቁ” አሉ አንጀታቸው ብግን እንዳለ ነው።

“እንደው ስንቱን እንለፈው እባካችሁ” አሉ ለራሳቸው።ወደ ድርጅታቸው በር እያመሩ። “እውን እኛም በዚህች አገር ላይ እኩል ዜጎች ነን ይባላል። እንዲያው ተወልደን ስላደግንባት ካልሆነ በስተቀር። እኩልማ አይደለንም... እራስን ማታለል ካልሆነ በስተቀር። ማዳበሪያ ሲባል እህል፤ እህል ሲባል መሬት፤ መሬት ሲባል የስራ እደል፤ የስራ እድል ሲባል ትምህርት.. እንደው ምኑ ቅጡ ሁሉ ነገር ለተደራጁ ብቻ።

“ድሮ ድሮ በደምና በአጥንት የተመረጡትና የተቀቡት ከዜጎች ሁሉ ልቀው ስለተገኙ ምርጥ ምርጡን እየመረጡ ተገለገሉብን። ቀጠሉና ባለቀይ ካርዶቹ ምርጥ ዜጎች ተብለው ነገሱብን። እኛንም ሀገራችንንም ገድለው በቁማችን ቀበሩን። ያኔስ እሺ ዘመኑ አልሰለጠነም አመራሩም አምባገነን ነበር እንበል። በዴሞክራሲና በእኩልነት ስም እየማሉና እየተገዘቱ፤ በዜግነት ለሚገኝ መብት ደርሶ መስፈርት መደርደር አሁን ምን ይሉታል። እንዴትስ ባልተጻፈ ሕግ ከዜጋም ዜጋ ይመረጥብናል። እንቆቅልሽ እኮ ነው።” ከራሳቸው ጋር ሙግቱን ቀጠሉ።

“እንደው እንደው መሪዎቻችን ሲያስቡት እንደምርጦቹ ሁሉ እኛስ የምንደፍነው ጉሮሮ የለምን? ከራሳችን ተርፈን ለሌላው የስራ እድል አልፈጠርንምን? ግብር በወቅቱ አልከፈልንምን? ከዜጋም ዜጋ ተመርጦ መሬት በነጻ! ብድር በዝቀተኛ ወለድ! አቀርቦት በርካሽ! እያደሉ እንዴት አድርገን ነው ከምርጦቹ ጋር ተወዳድረን ሰርተን የምንኖረው።” ጉዳዩን ባሰቡት ቁጥር እንቆቅልሹ እርሰ በርሱ እየተራባ ጭንቀላታቸውን ይበልጥ አዞረው።

ጭንቀላትህን ይዘህ ጩህ ጩህ አሰኛቸው። ዳሩ ማን ሰምቶ.....

ሰዓቱ እየረፈደ ስለመጣ ነው መሰል፤ ጸሀይዋም ደመናውን ገላልጣ ፍንትው ብላ ከመውጣቷ ማቃጠል ጀምራለች። የመኪናው ጡሩምባና ድምጽ፤ የሰዉ ጫጫታና ሁካታም እየበረከተ መጥቷል።

“እንደምን አደሩ አቶ ደጉ” የሰፈር ሰው በበራቸው ሲያልፍ ሲያገድም ሰላምታ ያቀርባላቸዋል።

በደመነብስ “እንደጊዜው እንደጊዜው።” መልስ ይሰጣሉ። “እውነትም እንደጊዜው.... ወቸው ጉድ ወድጄም አልነበር ለካ” አሉ አቶ ደጉ።

አንዴ ሽቅብ ደግሞ ቁልቁል አሉና ከግራ ቀኝ እየማተሩ የሚርመሰመሰውን የሰፈር ሰው በቅጡ መታዘብ ጀመሩ። በመጀመርያ አይናቸው ውስጥ የገቡት አቶ በድሉ ናቸው። አቶ በድሉ እንደለመዱት አቀርቅረው፤ እጃቸውን እያወናጨፉና ብቻቸውን እያወሩ ነበር የሚጓዙት።

“እንደምን አደርክ በድሉ።” ብለዋቸው መንገዳቸውን ቀጠሉ።

አቶ በድሉ በአዲሱ የቢፒአር አወቃቀር ምክንያት አለስፈላጊ ሆነው ከስራ ከተቀነሱ በኋላ በአንድ የግንባታ ድርጅት ውስጥ በካቦነት ተቀትረው ያገለግላሉ። እንደዛሬ አያድርገውና ቀጥ ብለው የሚሄዱ ንቁና ኩሩ ዜጋ ነበሩ። የመልካም አስተዳደር ሰለባ መሆናቸው ነው።

ቀጥሎ ያለፉት ወ/ሮ ሰብስቤ ሌላዋ የሰፈራቸው ነዋሪ ናቸው። ዛሬስ የረፈደባቸው ይመስላል፤ የሚራመዱት ፈጠን ፈጠን እያሉ ነው። ከሶስት ዓመት በፊት በሰፈሩ ወስጥ የታወቀ ጠላ ቤት የነበራቸው ደርባባ ወይዝሮ ነበሩ። የኢኮኖሚ እድገቱ የፈጠረው የዋጋ ግሽበት የቀሰቀሰው ድህነት የአካባቢውን ነዋሪ የመግዛት አቅም በማዳከሙና የእህል ዋጋ በመናሩ፤ ለሰፈሩ ነዋሪ በሚመጥን ዋጋ ጠላ ማቅረብ ባለመቻላቸው የጣላ ችርቻሮ ንግዳቸውን አቋርጠው በጉልት ቸርቻሪነት ተሰማርተዋል። የኢኮኖሚ እድገቱና የዋጋ ግሽበቱ ሰለባ መሆናቸው ነው።

ቀጥሎ ያለፉት የሰፈራቸው ነዋሪ ዶ/ር ድልነሳው ናቸው። ዶ/ር ድልነሳው እጅግ ዘመናዊ በሆነና መስኮቱ በጥቁር ከለላ በተጋረደ መኪና ነው የሚንቀሳቀሱት። ከዚህ ቀደም ቀንደኛ የቅንጅት ደጋፊ ነበሩ። በቅንጅት ግርግር ምክንያትም ትንሽ ተነሽመዋል፤ አልፎ ተርፎም ለጥቂት ጊዜም ቢሆን የከተማ ውስጥ እስር ቀምሰዋል። ያ ሁሉ አልፎ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንቱ የተባሉ የመንግስት ሹመኛ ሆነዋል። ዶ/ር ድልነሳው ከተቃዋሚ ጎራ ወደ ኢሕአዴግ ጎራ የተቀላቀሉበት ፍጥነት ለሰፈሩ ሰው አሁንም እንደትንግርት የሚወራ ጉድ ነው። የሚጠረጥሩቸው ሹመቱን ያገኙት እስር ቤት እያሉ የቅንጅትን መረጃ ለኢህአዴግ አሳልፈው በመስጠታቸው ነው እያሉ ያሟቸዋል። ሌሎች ደግሞ ዶክተሩ ቀድሞውንም ቢሁን በባህሪያቸው ጥቅመኛ ስለነበሩ ቅንጅት ካሸነፈ ሊሾሙ አቅደው እንጂ ቅንጅትን አምነውበት አልነበረም። ለዚህም ነው የቅንጅት መዳከምና መበታተን ተከትለው በፍጥነት ሿሚና ሸላሚ ወደ ሆነው ወደ ኢሕአዴግ “ሸርተት ያሉት” ይሏቸዋል። ኢሕአዴግም እንደ ቅንጅት የሰው ኋይል ችግር ስላለበት፤ ተፈጥሮው ባይፈቅድም አላሳፈራቸውም “በደላቸውን” ይቅር ብሎ ሾሞና ሸልሞ ለዚህ እንዳበቃቸው ይታማል። ግራም ነፈሰ ቀኝ ዶ/ር ድልነሳው ከኢሕአዴግ ጋር ልማታዊ ተልኳቸውን ለማሳካት ጊዜ ያጠራቸው ይመስል በተለመደው ፍጥነት ጠባቧን የሰፈራቸው መንገድ ሽው ብለው አለፏት። የመቻቻል ፖለቲካው ተጠቃሚ መሆናቸው ነው።

ብዙም ሳይቆይ አቶ ሐብታሙ ተከተሉ። እሳቸው ደግሞ የዘመኑ ሰው የሚባሉት ዓይነት ናቸው። ካለፉት ሶስትና አራት አመታት ወዲህ የኢኮኖሚ እድገቱንና የኑሮ ውድነቱን ተከትሎ ባካበቱት ሐብት ምክንያት ቢጠሩዋቸው የማይሰሙ የናጠጡ ዲታ ሆነዋል። እንደተለመደው በጥቁር መርሴደስ የቤት አውቶሞቢላቸው በጠባቧ መንገድ ላይ ቀስ ብለው ይፈሳሉ። ከአውቶሞቢላቸው ጀርባም “ንብን ይምረጡ” የሚል ስቲከር ለጥፈዋል። አቶ ሐብታሙ ዕድሜ ልካቸውን በጅምላ የሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ የተሰማሩ ቢሆኑም ቀን የወጣላቸው ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ ነው። በዋጋ ግሽበቱ ምክንያት ያልተረጋጋውን ገበያ ተጠቅመው በየመንግስት ተቋማቱ ከመሸጉ መሰሎቻቸው ጋር በመመሳጠር ሸቀጥ በማከማቸትና ጊዜያዊ እጥረት በመፍጠር ገደብ የሌለው ትርፍ ያካበቱ ናቸው። አቶ ሐብታሙ በዚህ ድርጊታቸው በርካታ ህዝብ ስላቆሰሉ፤ ኢህአዴግን እንደከላላ እየተጠቀሙበት እንደሆነ በሰፈሩ ውስጥ በሰፊው ይወራል፡፡ ከጥሪታቸውም ቀንሰው ለዚህ የምርጫ ቅስቀሳ የሚውል ዳጎስ ያለ ገንዘብ ለኢሕአዴግ ፈሰስ እንዳደረጉ ይታማሉ። አቶ ሐብታሙ ከኢኮኖሚ እድገትና የዋጋ ግሽበቱ ተጠቃሚ መሆናቸው ነው።

አቶ ደጉ በሰፈራቸው ውስጥ የሚኖሩና ስርዓቱ ያንኳለላቸው ስንት ወ/ሮ ሰብስቤ ስንት አቶ በድሉ? እንዳሉ በሌላ በኩል ደግሞ ስርዓቱ እንደአሸን ያፈላቸው ስንት ዶ/ር ድልነሳው ስንት አቶ ሐብታሙ እንዳሉ ማወቅ ባይቻላቸውም፤ ቁጥራቸው ግን ቀላል እንዳልሆነ ይገምታሉ።

"ብቻ ምኑ ቅጡ... ምኑ ቅጡ ብቻ... ስንቱ ተወግቶ ስንቱ ተረስቶ ይዘለቃል..." አሉ። አቶ ደጉ ቃላት ከአፋቸው አምልጦ።

አበራ "አቤት ጋሼ " አላቸው ግራ እንደተጋባ ነው።

በሁኔታቸው ትንሽ እንደማፈር ያሉት አቶ ደጉ ጥያቄውን በጥያቄ በመመለስ "ዛሬ ደግሞ ሰራተኞቹ ሁሉ ምን ሆነው ነው ስራ ያልገቡት" አሉ ሰዓታቸውን ተመልክተው።

ሰራተኞቻቸው መሬትና ብድር ለማግኘት በአነስተኛና ጥቃቅን ስለተደራጁ የኢሕአዴግ የምርጫ አደራጅ፤ ቀስቃሽና ጠርናፊ እንደሆኑ እያወቁ ለምን እንደጠየቁት ገርሞት ቀና በሎ አያቸው።

" ዛሬ የሙብራት ተረኞች ስለሆንን ስራ የለም ብለው እንደተለመደው ለቅስቀሳ ሄደዋል።" አላቸው ከዝምታቸው መልስ እየጠበቁ እንደሆነ ስለተረዳ።

"ወቸው ጉድ ሙብራት የለም ! ውኋ የለም ! ሰራተኛ የለም! ጤና የለም! እህስ ልማትና ምርጫ ብቻ። ጉዳዩ እንዲህ ከሆን እንግዲህ ምን ይደረጋል ይቻላል ወደ ቤቴ ሔጀ ልረፍ እንጂ" አሉ ቀቢጸ ተስፋ ባጠላበት መንፈስ።

"አበራ በል እንግዲህ በሩን ቆላልፍና አንተም ወደምትሔድበት ሒድ።" አሉት

አበራ ዛሬ ያስተዋለው የአቶ ደጉ ባህሪ ግር እንዳለው ነው። አይቶባቸው የማያውቀው ባህርይ በመሆኑ ስጋት ገብቶታል። ብቻቸውን እያወሩ ከፊቱ እስኪሰወሩ ድረስ ቆሞ ታዘባቸው። በልቡ- ያበደው እኔ ነኝ ዘመኑ ሳይል አልቀረም ።

አቶ ደጉ ሰፈራቸው ወደሚገኘው ልማት ቡና ቤት ጎራ ብለው የተቃጠለ አንጀታቸውን በቀዘቀዘ ድራፍት ማራስ አሰኛቸው። ግን ምን ያደርጋል ጊዜው ገና ከጠዋቱ አምስት ሰዓት ላይ ነው... አገሩስ ምን ይላል ?

ከፊታቸው የሚመጣው መንገደኛ ሁሉ አቀርቅሮ ወረቀት እያነበበ ያልፋል። በቅርብ ርቀት ቆሞ የሚታያቸው አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ ቀስቃሽ በራሪ ወረቀት ያድላል። በዚህ መሐል የተቃዋሚው ቀስቃሽ እዛ አካባቢ መኖሩ መረጃ የደረሰው ይመስል ከየት መጣ ሳይባል በድንገት የደረሰው የኢህአዴግ ቀስቃሽ ሚኒባስ እንደደረሰ፤ በድምጽ ማጉያው የንቦችን ቅስቀሳ እያስተጋባ አካባቢውን አደበላለቀው።

"... ጊዜው የልማትና የሰላም ነው። ልማታችንን ድንጋይ ፈለጣ! ሲሚንቶ ጥፍጠፋ! ሊጥ ጋገራ! እያሉ የሚያንቋሽሹ ተቃዋሚዎችን መምረጥ ፀረ-ልማትና ፀረ-ሰላማዊነት ነው..."

የተቃዋሚውን እጩ ከበው ወረቀት ይቀበሉ የነበሩት ሰዎች በሁኔታው ተደናግጠው ከመቅጸበት ብትንትን አሉ። የሚኒባሱ ተናጋሪ ንግግሩን ጋብ አደረገና ዘፈኑን ለቀቀው... የሰፈሩ ሰው እንዳቀረቀረ ግራና ቀኝ የቆሙትን የተቃዋሚና የንብ ቀስቃሾች እንዳላየ ሆኖ ወደ ጉዳዩ መንገዱን ቀጠለ።

ሚኒባሱ ከስምንት በላይ ሰዎችን ጭኖአል። አቶ ደጉ ሁሉንም በዓይን ያውቋቸዋል። በተለያየ ምክንያት የሚታወቁ ዝነኛ የሰፈር ልጆች ናቸው። ቢያንስ ስድስቱ የቀድሞው ቅንጅት ነውጣኛ ቀስቃሾች ነበሩ። ከዚህ ቀደም በአደገኛ ቦዘኔነት የታሰሩም አሉበት።

“ልማት…ፀረ-ልማት፤ ሰላም…ፀረ-ሰላም…” መፈክሩና ዘፈኑ ቀጥሏል። የተቃዋሚው ቀስቃሽ የተሸማቀቀና የደነዘዘ ይመስል ወረቀት ማደሉን አቁሞ በትዝብት የንብ ቀስቃሹን ሚኒባስ ይመለከታል።

አቶ ደጉ የተቃዋሚውን ቀስቃሽ ጠጋ ብለው “አይዞህ ነቃ በል እንጂ መብትህ አይደለም እንዴ?” አሉት በራሪ ወረቀቱን እየተቀበሉና ትከሻውን እየዳበሱ። ሚኒባሱ ውስጥ ያሉት ቀስቃሾች ዘፈኑን ጋብ አድርገው ማስጠንቀቂያ በሚመስል ድምጽ ወደ መፈክሩ ተመለሱ።

“ተቃዋሚን መምረጥ ልማትን ማደናቀፍ ነው! ሰላምን ማደፍረስ ነው! … የተለያዩ መሰረተ ልማቶች እየተከናወኑ ይገኛል። በአነስተኛና ጥቃቅን ያልታቀፉ እንዲታቀፉ ሁኔታው ይመቻቻል! ከልማቱ ያልተጠቀመ ይጠቀማል!”

አቶ ደጉ ሰምተው እንዳልሰሙ በመሆን ወረቀቱን አጣጥፈው ኪሳቸው ከተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። “ልማት… ፀረ-ልማት፤ ሰላም… ፀረ ሰላም” ቅስቀሳው እየራቃቸው እየራቃቸው በዛው ጠፋ።

አቶ ደጉ ጉዞቸውን ቀጥለው የሰፈራቸውን መገንጠያ እንደጀመሩ ከሰፈራቸው መግቢያ ደልዳላው ስፍራ ላይ ድንኳን ተጥሎ ሲመለከቱ ክው አሉ።

“በስማአብ ወወልድ..” ብለው አማተቡ። አሁን በሰላም አልነበር ከሰፈር የወጣሁት ደግሞ ማን ሞተ? ጭንቀላታቸው በውጥረት እስኪፈነዳ ድረስ በሰፈሩ ውስጥ የታመመውን ሰው ሁሉ አንዴ ቃኙ።

ፈጠን ፈጠን ባለ እርምጃ ገስግሰው ወደ ድንኳኑ ተጠጉ። ድንኳኑ በሰንደቅ ዓላማ አጊጦል። የሞተው አርበኛ ይሆን እንዴ? አሰብ አደረጉ። ድንኳኑ በር ላይ የቀበሌያቸው የሴቶች ጉዳይ ሃላፊ የሆኑት ወ/ሮ ትብለጽ የክት ልብሳቸውን እንደለበሱ ድንኳኑ ደጃፍ ላይ ቆመዋል።

እንዴት ነው ነገሩ! አቶ ደጉ ይበልጥ ግራ ገባቸው። ድንኳኑን ጠጋ ብለው ወደ ውስጥ ተመለከቱ። አግዳሚ ወንበር ተደርድሯል፤ ሰው ግን የለም። ቀና ብለው ተመለከቱ ድንኳኑም ወንበሩም ያው የሚያውቁት የወዛደር መረዳጃ እድር ንብረቶች ናቸው። እግራቸው መራመዱን አላቆመ ኖሮ ስለጉዳዩ ልጠይቅ አልጠይቅ እያሉ እንዳመናቱ ድንኳኑን አልፈው ወደ ቤታቸው ታጠፉ።

በራቸውና አጥራቸው ንብን ይምረጡ! አበባን ይምረጡ! ጣትን-እጅን ይምረጡ! በሚሉ ፖስተሮች ተለጣጥፏል። ከምርጫው ጋጋታ ጋር በተያያዘ ቀኑን ሙሉ ያዩትና የሰሙት ተደማምሮ ቤታቸው ድረስ ሲመጣ ሁሉም ነገሩ እጅ እጅ ብሏቸዋል። የዜግነት መብታቸውን የተነጠቁ ያህል ስለተሰማቸው ናላቸው ዞሯል። እንደገና አይናቸውን እንደመያዝ እያደረጋቸው ነው።

የአጥር በራቸው እንደተከፈተ እግራቸው እንኳን ሳይገባ። “ይህ ሁሉ ቤቴ ላይ ሲፈጸም የት ነበራችሁ!” አሉ ሳግ በተናነቀው ድምጽ።

“ምኑ?” አለች የቤት ሰራተኛዋ፡፡

“ይህ ሁሉ ወረቀት ምንድን ነው”

“የቱ!” አለችና ሰራተኛቸው አንገቷን አስግጋ ወደ ውጭ ተመለከተች።

አጥሩ አንድም አልቀረ ፖስተር ብቻ ነው። “ጋሼ እነዚህ ኮቴ ቢሶች ናቸው እኮ። አንዳቸውንም አልሰማናቸውም !” አለች

“ አንቺ ስታንቀላፊ ። ባለቤት የሌለው ቤት አግኝተው እነሱ ምን ያድርጉ።”

ነገሩን ሁሉ ከባለቤታቸው ለመረዳት የፈለጉ ይመስል ጮህ ብለው መጣራት ያዙ “ዙሪያሽ! አንቺ ዙሪያሽ ”

“እትዬ የሉም።” አለች ሰራተኛዋ።”

“ ገና በጠዋቱ ደግሞ ወዴት ሔደች።”

“ቀበሌዎች ጠርተውኛል ሲሉ ነበር ምን አልባት እዛ ይሆናሉ።”

“ወቸው ጉድ! እንዴት አልነገረችኝም? ለካስ ዘንድሮ በሀገር ጉደይ ብቻ አይደለም ባዕድ የሆንኩት። በቤቴም ጉዳይ ነው።” ሲሉ አጉተመተሙ።

አቶ ደጉ ግራ እንደተጋቡ ወደ ሰራተኛዋ ዞር አሉና “እዚህ ሰፈራችን ማዞርያ ላይ የተተከለው ድንኳን ምንድን ነው” አሏት። ድምጻቸው ሌላ ጉድ ለመስማት በመፈለግና ባለመፈለግ መካከል የተሳቀቀ ዓይነት ነው።

“ቡና ጠጡ ነዋ!” አባባሏ አልሰሙም እንጄ ይመስላል።

የምታሾፍባቸው ስለመሰላቸው ደማቸው ይበልጥ ከፍ ማለቱ እስኪሰማቸው ድረስ እየተበሳጩ “የምን ቡና ጠጡ ነው! ቀልድ ነው የያዝሽው?” ሲሉ አፈጠጡ።

“የኢህአዴግ ነዋ! በየሰፈሩ የቀበሌ አመራሮችና ጠርናፊዎች ሰዉን በአምስት በአምስት አደራጅተው ሲያበቁ እየዞሩ ቡና ጠጡ እያሉ ሲቀሰቅሱ ነው እኮ የሚውሉት።”

“እኛ ጋ መጥተው ነበር ማለት ነው?”

“በየቀኑ እኮ ነው የሚመጡት ጋሼ። ሌላም ስራ ያላቸው አይምስልም። በየቀኑ ጠዋት ጠዋት የሰው በር ማንኳኳት፡፡ መዝገብ ይዞ ካርድ ወስደሃል ወይ? ማንን ነው የምትመርጠው? ኢሕአዴግን ምረጥ... ማፋጠጥ ነው። ከዛ ደግሞ ፈርምልኝ... እንደው እኮ መላ ቅጡ የጠፋው ነገር ነው። በአንድ በኩል የምትፈልጉትን ምረጡ እያሉ ይቀሰቅሱናል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በየቤቱ እየዞሩ ማንን እንደምትመርጥ ንገረን እያሉ ያፋጥጡናል። እንደው ሳር ቅጠሉ ሁሉ እኮ ነው የሰለቻቸው። አሁንስ ሰዉ ሁሉ ምርጫ የሚባል ነገር እንደው ባልመጣ እያለ ነው!”

አቶ ደጉ በጥሞና ሲያዳምጧት ቆይተው የነገረቻቸውን እያብሰለሰሉ “ ታድያ መምጣታቸውን ለምን አልነገራችሁኝም።” አሏት።

“እንደው የነሱ ነገር እምብዛም ስለማይጥምዎትና ጊዜ ስለሌለዎት ብለን ነው” አለች

“ቡና ጠጡ.. ቡና ጠጡ...” ቃሉን እያሰላሰሉ ቆዩ ። ቡና ጠጡ ምን ማለት ይሆን? “ይህንንማ ጉድ ማየት አለብኝ” አሉና “ለመሆኑ ቡና የሚጠጣው መች መች ነው?” ጠየቋት

“ምን ቅጥ አለው ጌታዬ! አንዳንዴ ቀኑን ሙሉ ነው። ሲያሻቸው ደግሞ በምሳ ያደርጉታል። ደመቅ የሚለው ግን ማምሻው ላይ ነው።” ንግግሯ የመቋመጥ ዜማ አለው።

“ይህን ሁሉ እንዴት አወቅሽ፤ ትሄጂ ነበር ማለት ነው?” አፋጠጧት።

“አዎ ጋሼ። እትዬ ልከውኝ ሄጄ ነበር።”

“ትቀጥፊያለሽ እንዴ ድንኳኑ የተተከለው ዛሬ አይደለም?”

“ቡና ጠጡ የተጀመረው በቀበሌ ጊቢ ውስጥ ነበር፣ በድንኳን መካሄድ የተጀመረው ሰሞኑን ነው።” መለሰች።

እንዴት ነው ነገሩ እንደዚህ ያለ ቅጥ ያጣ መደበላለቅ። ቀበሌ ደግሞ ከመቼ ጀምሮ ነው ቡና አጣጪ የሆነ።

“መጀመሪያ የራሳቸውን ስራ በቅጡ ቢወጡ ደግ ነበር፣ ቡና እያንቃረሩ ሰዉን ስራ ከሚያስፈቱ!” አሉና አቶ ደጉ አሰብ አድርገው “እንደው ይሄ ቀበሌ የሚባል ተቋም ዝንተ ዓለሙን የገዢዎች መሳሪያ ሆኖ ከማገልገል ያለፈ ሚና የለውም ማለት ነው። በቀድሞው ስርዓት አንዴ ጠቋሚ ሌላ ጊዜ አስጠቋሚ እየሆነ... ሲሻው በመግደል ሲያሻው በማስገደል ተግባር ላይ ተሰማርቶ በዚሁ የተላላኪነት ባህሪው አንድ ትውልድ ገድሎ ለገዳይ ሰጠ። ያ ሳያርመው ከርሞ፤ አሁን ደግሞ በቡና አጣጪነት ተግባር ላይ ተሰማርቶ ሕዝቡን ግራ ማጋባቱ ምን ይሉታል። ነገሩ ሁሉ ከንዴትም አልፎ አልዋጥ አላቸው። በዚህ ከቀጠለ በክፉ ቀን የቀበሌ ሚና ምን ሊሆን እንደሚችል ሲታሰባቸው ሰውነታቸውን ዝግንን የሚያደርግ ወረርሽኝ ለቀቀባቸው።

“ታድያ እስካሁን ቀበሌ ምን ታደርጋለ?”

“ባለፈው ቀን ጠርናፊዎቹ ቤት ድረስ መጥተው ሰራተኛ እንዴት ይልካሉ ንቀት ይመስልብዎታል። ሲሆን አቶ ደጉ አልያም እርስዎ መምጣት ነበረብዎት ስላሏቸው፣ ይህንኑን ለማስተባባል ይመስለኛል አንግዲህ...ብቻ እንጃ።” ቀጠለች “ባለፈውም ባለሽቀጥ ቤትዋ ሴትዮ ቡና ጠጡ ላይ ባትቀሩ ይሻለል። እንኳን እናንተ ተራውም ሰው ሲቀር ይታወቃል ስላሉኝ ፤ይህንኑ ነግሪያቸዋለሁ። በዚህም የሰጉ ይመስለኛል።”

"እንደው የዚህ አገር እጣ ፈንታ እንዲህ ሆኖ መቅረቱ ነው።" አሉ። "የአፋሽ አጎንባሹ፣ የቃል አቀባዩ፣ ወሬ አመላላሹ መብዛት እያስደነቃቸው።

"እንደው ለመሆኑ ባለሱቋ በኔ ቤትና ህይወት ምን ጥልቅ አድርጓቸው ነው ደርሶ መካሪ የሆኑት። እኔ የምለው አማካሪ ያስፈልገኛል ብዬ አውጃለሁ እንዴ.. ወይስ ማስፈራራታቸው ይሆን። ህምም.. ማስፈራራት!" አቶ ደጉ ትንፋሽ እንዳጠራቸው ናቸው።

"በይ አሁን ሳሎኑን ከፈቺልኝና ልረፍበት።" አቶ ደጉ በልባቸው አንቺስ ብትሁኚ ምንሽ ይታመናል በሚል የጥርጣሬ መንፈስ እንደተሞሉ ናቸው። እንደው አሁን ይህንን ሁሉ አሉባልታ ያለነገር ታጠቀች ፤ አምታ እያሳማችን ቢሁን እንጂ... በልባቸው አጉተመተሙ።

ቀኑ ደንገዝገዝ ሲል አቶ ደጉ ቡና ጠጡን ለማየት ወደ ድንኳኑ አመሩ። በርቀት ዘፈን ደማቅ ይሰማል..

"ብሔር.. ብሔረሰቦች ብሔረሰቦች

ኑ ኑ የኢትዮጵያ ልጆች የኢትዮጵያ ልጆች...".

እነዚህ ጥሪ የሚደረግላቸው የኢትዮጵያ ልጆች እነማን ይሆኑ? የትስ ይሆን የሚገኙት? የሚል ጥያቄ አጫረባቸው። መዝሙሩ የሚሰብ ዜማ ስላለው፤ ሳያስቡት ዜማውን በልባቸው እያዜሙ ወደ ድንኳኑ ዘለቁ ። አቶ ደጉ በጀነሬተር ኋይል በሚበራው የፍሎረሰንት ብርሀን ድንኳኑን ለመቃኘት ሞከሩ። ጥግ ጥጉን ይዞ በተደረደረው አግዳሚ ወንበር ላይ ቀላል የማይባሉ የሰፈሩ ሰዎች ሐብታም ድሃ ሳይል ተኮልኩለዋል። የሐይማኖት መሪዎችም አልቀሩም። ብዙዎቹን በአይን ያውቋቸዋል። አንዳንዶቹ ያደረጉት ኮፍያ ዝቅ እያደረጉ ቀሪዎቹ ደግሞ አንገታቸውን እየወዘወዙ ሰላምታ ሰጧቸው።

የቀበሌያቸው የሴቶች ጉዳይ ሃላፊ የሆኑት ወ/ሮ ትብለጽ አንዳች በሚያህል ረከቦት ላይ የደረደሩትን ሲኒዎች ጫጩቶቿን እንደምትንከባከብ ዶሮ አቅፋቸው ተቀምጣለች። በስተግራ ሲል በትልቅ ምድጃ ላይ የተጣደው ጀበና በደነፋ ቁጥር በአናቱ እንፋሎትና ቡና ይደፍቀዋል ።

አቶ ደጉ ሲገቡ የተፈጠረውን የዝምታ ድባብ ለመስበር ያቀደ ይመስል የሰፈራቸው ታዋቂ ቀልደኛ ማሩ "ዛሬ እንዴት ነው አቶ ደጉ ብቅ አሉሳ? የሚገርም ነው። አቶ ግሩምም መጥተው ነበር!" አላቸው። አቶ ግሩም የታወቀላቸው የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊ ናቸው።

አቶ ማሩ የተናገረው ነገር ይበልጥ እፍረትና መሸማቀቅ በድንኳኑ ውስጥ ስለፈጠረ ቡና ጠጭው በሙሉ አንዴ ፊቱን ወደሱ አዙሮ አፍህን ዝጋ የሚል ይመስላል። አፈጠጠበት።

አቶ ደጉ አዳሜ ሁላ ስታሚኝ ከርመሻል ማለት ነው ሲሉ አሰቡ። ለአስተያየቱ ምንም መልስ ሳይሰጡ አለፉት።

"አቶ ደጉ ቡናው ፈልቷል። በስኳር ይሁንሎት ያለስኳር... " ጠየቀች ወ/ሮ ትብለጽ።

አቶ ደጉ "ያለስኳር" አሉ

ቀሪው ተዳሚ በግሉ ወሬው ስለተጠመደ ጫጫታው እየበረከተ መጣ። አቶ ደጉ ታዳሚውን በድጋሚ ለማዳመጥ ሞከሩ። ሰዉ ሁሉ ቅጥ ያለው ነገር የሚያወራ አይመስልም። እንዲያው ብቻ በየጎራው በየጎራው ተቧድኖ በየግል ጉዳዩ አፍ ገጥሞ ሮሮና ብሶቱን ያውካካል። ቡና ጠጡው እንደተለመደው የአሉባልታ ማሳላጫነቱን ተግባር እየተወጣ ነው።

ምን ጉድ ነው። አሉ አቶ ደጉ በግራ ቢዞሩ ብሶትና ሮሮ በቀኝ ቢዞሩ ብሶትና ሮሮ.. የኑሮ ውድነት፤ የግብር መብዛት፤ በየአገልግሎት መስጫው መጉላላት፣ ስራ-አጥነት፣ መብራት መጥፋት... እንደው ስራና ሰዎ ብቻ ሳይሆን ሀገሩም ጭምር ቆሟል ማለት ነው...

ሀሳባቸውን ሳያጠናቅቁ የሚጠበቁት እንግዳ የኢሕአዴግ እጩ ተወዳዳሪ ወደ ድንኳኑ ገቡ። በርካታ ንብ የሰፈረበት ቢጫ ጃኬት ለብሰዋል። ቢጫ ኮፍያም አጥልቀዋል።

ታዳሚው ከተቀመጠበት ተነስቶ ማጨብጨብ ሲጀምር እጩ ተወዳዳሪው ኮፍያቸውን ከፍ ዝቅ እያደረጉ “ ኧረ አይገባም...ኧረ አይገባም... ተቀመጡ... ተቀመጡ!” ሲሉ አግደረደሩ።

ወ/ሮ ትብለጽ በቆሙበት ንግግራቸውን ጀመሩ “የተከበራችሁ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎች የዘንድሮው ምርጫ አንድም ቀዳዳና ክፍተት በሌለው መልኩ በድል ለማጠናቀቅ እንዲቻል የተለያዩ ጥረቶችን ስናደርግ ቆይተናል። በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ በገንዘብም ሆነ በተለያየ መንገድ ያልተቆጠበ ጥረታችሁን እገዛችሁን ላደረጋችሁልን ደጋፊዎቻችን ምስጋናችን ከልብ ነው።”

ሞቅ ያለ ጭብጨባ ተከተለ።

“... ተቃዋሚዎች ተደራሽ የሆነውንና በጅምር ላይ የሚገኘውን ልማታችንንና የተረጋጋውን ሰላማችንን ከማደፍረስ ያለፈ ሚና እንደሌላቸው ይታወቃል፤ ይልቁኑ የተላላኪነት ሚናቸውን ተጠቅመው ልማታችንንና ሰላማችንን እንዳያደናቅፉ...”

ጭብጨባ ቀጠለ...

እንደው ይሄ ልማት ከስንት ዓመት በኋላ ይሆን ከጅምርነት የሚላቀቀው። መቼ ይሆን ወቀሳውና ማሸማቀቁ በቀናንት የሚተካው። እንደው አሁን እስኪ መድረክ ተገኘ ህዝብ ተሰበሰበ ብሎ ድርሶ ውርጅብኝ ማዝነብስ ለማን ይበጃል። እንደዚህ አይነቱ ተግበር ቀድመው ለተራቀቁበት ለኢሰፓዎቹም አልበጀ።

ተጨማሪ ለማዳመጥ ያልፈለጉ ይመስል። አቶ ደጉ ሹክክ ብለው ከውንበራቸው በመነሳት ወደ ድንኳኑ መውጫ አቀኑ። ቀኑን ሙሉ ከምርቃቱም፣ ከስድቡም፣ ከማስፈራራቱም ቱፍታ ተቋድሰዋል። ሁሉን የጠገቡ ይመስላሉ። ቆም አሉና እንደመሳቅ በለው “ልማትና ብሶት” የዘንድሮ ምርጫ መሪ መፈክር መሆን ነበረበት አሉ ለራሳቸው።

በስራ-አጥነት፣ በኑሮ-ውድነት፣ በኪራይ ሰብሳቢነት የተተበተበው “ልማታዊው የኢሕአዴግ የምርጫ ጥሪ” ከጉሮሯቸው አልወርድ እንዳይልና ከሰው ተለይተው እንዳይቀሩ በመስጋት ልማት ሆቴል ገብተው በልማታዊ ድራፍት የተናነቃቸውን ማወራረድ ስለፈለጉ ወደ ልማት ቡና ቤት አመሩ።

ልማት ቡና ቤት ውስጥ መብራት የለም። ከወትሮው ውጭ አዲስ ነገር ቢኖር በፋኖሱ ብርሃን የሚታየው የኢህአዴግ የምረጡኝ ፖስተር ብቻ ነው።

“ማን ቀረ እንግዲህ።” አሉ። አቶ ደጉ አምላካቸውንም የጠረጠሩ ይመስል ወደ ሰማይ ቀና ብለው አያዩ። ከኪራይ ሰብሳቢው ጀምሮ እስከ ልማት ሰለባው ድረስ ሁሉም ከኢህአዴግ ጋር ወደፊትን እየዘመረ ነው! ዴሞክራሲና ጸረ-ዴሞክራሲ፤ ሰላምና ፀረ-ሰላም፣ ልማትና ፀረ-ልማት ተደበላልቀዋል። ደግሞስ ዴሞክራሲና ጸረ-ዴሞክራሲ፤ ሰላምና ፀረ-ሰላም፣ ልማትና ፀረ-ልማት ተወዳድረው ዴሞክራሲን፣ ሰለምና ልማትን ሕዝቡ በነቂስ መደገፉ ሳይታለም የተፈታ ነው፤ ድሮውንስ ምርጫ ምን ያደርግ ነበር።

ዘንደሮ እንግዲህ ጉዳዩ እንዲህም አይደል። እንግዲያው። አሉ አቶ ደጉ ልማት ቡና ቤት እንደገቡ “በል አንተ ልጅ ! ማነህሳ! አንድ ልማታዊ ድራፍት አምጣ!” ከህዝብ ማን ይለያል። በልጠ መገኘት ነው እንጂ!

አቶ ደጉ የምርጫው ዕለት እንደተለመደው ሽክ ብለውና ከሰው ሁሉ ቀድመው ማልደው በመነሳት ነበር ለምርጫው የወጡት። ጋራ ሸንተረሩ ሁሉ “እሰይ እሰይ… ምኞቴ ተሳካ ልማቴ ቀጠለ!” የሚል ይመስላል።

አቶ ደጉ ሲያስታውሱት እንደማንኛውም ዜጋ መምረጣቸው ትዝ ይላቸዋል።ብቻ ግር የሚላቸው ነገር አለ፤ የመረጡትን ለልባቸውም ስላልነገሩት ነው መሰል፤ ማንን እንደመረጡ አያስታውሱም። ብቻ ቁም ነገሩ በምርጫው መሳተፋቸው ነው። መምረጣቸውንም ማስታወሳቸው ነው። ማን ያውቃል የወደፊቱን…

አቶ ደጉ ወደ መዝሙራቸው ተመለሱ።

“…ብሔር ብሔረሰቦች ብሔረሰቦች

ኑ! ኑ! የኢትዮጵያ ልጆች.. የኢትዮጵያ ልጆች…”

በመሐል የመዝሙራቸው ዜማ ተለወጠና ከፊታቸው በሚጨፍሩት በአዲሱ ትውልድ ተተካ

“… መጣና መጣና እኛም መጣና

ክፈት በለው በሩን የጌታዬን…”

የቡሔ ልጆች ቀጠሉ “…ዓመት አውድ ዓመት ድገምና ዓመት ድገምና፤

በየአምስት ዓመት፤ ድገምና ዓመት ድገምና

በእማምዬ ቤት፤ ዓመት ድገምና ዓመት

ወርቅ ይፍሰስበት ድገምና ዓመት ድገምና

ልማት በስንዴ ልማት በጤፍ ምቀኛህ …”